የሰ/መ/ቁ.47551

ታህሣሥ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ንግድ ማተሚያ ድርጅት - ነ/ፈጅ ጌታቸው ብርሃኑ

**ተጠሪ፡-** አቶ ካሱ ሙላት - ቀረቡ

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ያለ አግባብ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን በመግለጽ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለቀረበው ክስ በሰጠው መልስ ተጠሪ ለ6 ተከታታይ ቀናት ከስራ በመቅረታቸው ከስራ እንደተሰናበቱ በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲሆንለት አመልክቷል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ ከስራ ታመው የቀሩ መሆኑን ቢገልፁም ታመው ስለመቅረታቸው ማስረጃ እንዲያቀረቡ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጠይቀው ማቅረብ አልቻሉም፣ ያቀረቡት የሕክምና ማስረጃ በወቅቱ ያልቀረበና ከስራ ከተሰናበቱ በኋላ የተፃፈ ስለሆነ ከስራ የተሰናበቱት በአግባቡ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው ለማስረዳት የቀረበው አንደኛው ማስረጃ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የሌለው የትርፍ ሰአት ክፍያ የሚመለከት ነው፡፡ ሁለተኛው ማስረጃ የዲሲ□ሊን ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ ሲሆን አንድ ሰራተኛ ቀሪ መሆኑን ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባው የሰነድ ማስረጃ እንጂ የዲሲ□ሊን ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ ስላልሆነ ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ የ6 ወር ደሞዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት በህገ-ወጥ መንገድ ነው በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ተጠሪ በስር ክሳቸው በህመም ምክንያት ከስራ በመቅረታቸው አመልካች ያለአግባብ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ከስራ የተሰናበቱት ለ6 ተከታታይ ቀናት ከስራ ስለቀሩ መሆኑን ተከራክሯል፡፡ ከክርክሩ ሂደት እደተረዳነው ተጠሪ ከስራ መቅረታቸውን አልካዱም፡፡ ክርክራቸው የቀሩት በህመም ምክንያት ነው የሚል ነው፡፡ ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ግልባጭ በህመም ምክንያት ከስራ ለመቅረታቸው ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ማቅረብ አለመቻላቸውን ተረድተናል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ቢሆን ተጠሪ ማስረጃቸውን ለዲሲፕሊን ኮሚቴ አቅርበዋል አላለም፡፡ ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የአንድን ሰራተኛ ከስራ መቅረት ማስረዳት የሚቻለው በሰነድ ማስረጃ እንጂ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ አይደለም የሚል ነው፡፡ በመሰረቱ ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው ክደው አልተከራከሩም፡፡ የሚከራከሩት ከስራ የቀሩት በህመም መክንያት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በህመም ምክንያት ስለመቅረታቸው የማስረዳት ሸክም ያለባቸው ተጠሪው ናቸው፡፡ ተጠሪ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ማቅረብ አለመቻላቸው በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ከዛ በኂላ ደግሞ ያቀረቡት ማስረጃ ከስራ ከተሰናበቱ በኂላ የተፃፈና እጅግ ዘግይቶ የቀረበ ማስረጃ ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ ፍሬ ነገር ለማስረዳት ተለይቶ የተመለከተ ማስረጃ እንዲቀርብ ህጉ ካላስገደደ በቀር ይህን ፍሬ ነገር በማንኛውም የማስረጃ አይነት ከማስረዳት የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ በማስረጃነት ሊቀርብ የማይገባበትን የሕግ መሰረት አልገለፀም፡፡ ቢያንስ ማስረጃንውን መዝኖ ተጠሪ ከስራ ስለመቅረታቸው በበቂ ሁኔታ ማስረዳት የሚችል መሆን አለመሆኑን ሊመዝን ይገባ ነበር፡፡ በመሆኑም በማስረጃነት ሊቀርብ የማይችልበትን ምክንያት ሳይገልጽ በድፍኑ ቃለ-ጉባኤው ሊቀርብ የማይችል ማስረጃ ነው በሚል ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ

ሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከስራ የቀሩት በህመም ምክንያት መሆኑን ቢገልፁም ይህን ሳያስረዱ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 79174 ሰኔ 12 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27244 መጋቢት 14 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ